**ዶ/ር ሰይፋ ትርፌ**
በኢትዮጵያ የአይ.ኦ.ሲ.ሲ ተወካይ

# ኢትዮጵያንና አዘርባጃንን የሚያመሳስላቸው ምንድን ነው?

ከሁለት አሠርት በፊት አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ስለ አዘርባጃን ስለምትባለው አገር የሚያውቁት ከአርሜኒያ ናጎርኖ-ካራባክ የአዘርባጃን ክልል ወረራ ግጭት በዜና የሰሙትን ብቻ እንደነበር አምናለሁ፡፡ ጦርነቱ በ80ዎቹ መጨረሻ ከመጀመሩ በፊት በኢትዮጵያ ስለአዘርባጃን የሚሰማው ወይም የሚታወቀው በጣም ጥቂት ነበር፡፡

ሆኖም ባለፉት አምስት አመታት አዘርባጃን በአዲስ አበባ ኤምባሲዋን ከፍታለች፣ በአለም ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ባህል የአገሪቱን ሚና ለማስፋፋት ኤምባሲው ጉልህ ሥራዎች አከነውኗል፡፡ በተለይ በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የባህልና የትምህርት ግንኙነት ከማጠናከርና ስትራቴጂያዊ ከማድረግ አንጻር ጉልህ ጥረት ተደርጓል፡፡

በአዘርባጃንና በኢትዮጵያ (አዘርባጃኒዎች ሃበሺስታን በሚሏት ኢትዮጵያ) መካከል ከ12ኛው ክፍለ ዘመን የሚጀምር ረጅም ታሪክ ያለው ግንኙነት እንደነበረ ገና በቅርቡ መረዳት ችያለሁ፡፡ **“የባህል ብዝኃነትና የኃይማኖት መቻቻል በአዘርባጃን”** በሚል ርዕስ በ2018 መጨረሻ ላይ መደበኛ የምርምር ሥራ በምሠራበት ወቅት የ12ኛው ክፍለ ዘመን ታዋቂ የአዘርባጃን ባለቅኔ ሙጂራዲን ቤይላጋኒ (ከ113—1194) ወላጅ እናት ከኢትዮጵያ (ከሃበሺስታን) የመጣች መሆኑን የሚገልጽ ሥነ ጽሁፍ አጋጥሞኝ ነበር፡፡ ሆኖም በተለይ ከዚህ አስደናቂ የህዳሴ ዘመን የተያያዘ ዝርዝር ይገኙ እንደምመለስ ቃል የምገባ ቢሆንም በዚህ መጣጥፍ በአንጻራዊ ሁኔታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሁለቱ አገሮች መካከል ባለው ግንኙነት ላይ አሁንም የቀድሞዋ ሶቪየት ሕብረት አካል የነበረችው አዘርባጃን በወቅቱ ከሶቪየት ሕብረት ነጻነቷን ከተቀዳጀች በኋላም ጭምር በኢትዮጵያ በትምህርት ዘርፍ ስለነበራት አስተዋጽኦ የሚታወቀው በጣም ጥቂት መሆኑን አምናለሁ፡፡ በአዘርባጃን የከፍተኛ ትምህርት ሥርአት በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ከሆኑ የኢትዮጵያ ዜጎች አንዱ እንደመሆኔ በአዘርባጃን በተማሩና በሚኖሩ በመቶዎች በሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሥም ምስክርነቴን ለመስጠት እወዳለሁ፡፡ በተጨማሪም በሁለቱ አገሮች መካከልና በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ስላለው ግንኙነት የተሻለ ግንዛቤ ለመፍጠር በሚደረገው በዚህ እንቅስቃሴ ሌሎች ተሳታፊ ሆነው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ እጋብዛለሁ፡፡

ትክክለኛው አሃዝ ተጨማሪ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም ባለፈውና በዚህ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አንድ መቶ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ወደ አዘርባጃን የከፍተኛ ትምህርት ሥርአት የተላኩ መሆኑን፣ ይህም በ1970ዎቹ በኢትዮጵያና በሶቪየት ሕብረት መካከል ለተፈጠረው የርዕዮተ አለም፣ የኢኮኖሚና የባህል ግንኙነት መነሻ መሆኑን አምናለሁ፡፡ ባሁኑ ጊዜ





በኢትዮጵያ የሚኖሩና በኢትዮጵያ የአዘርባጃን ኤምባሲ የተመዘገቡ በአዘርባጃን ዩኒቨርሲቲዎች የተማሩ ከ65 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን አሉ፡፡ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በአዘርባጃን አጠናቀው ወደአገራቸው ያልተመለሱና የተሻለ እድል ፍለጋ በመላው አለም ተበታትነው የሚኖሩ ብዙ የቀድሞ የአዘርባጃን ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችም ይገኛሉ፡፡

አዘርባጃን በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተወዳጅ የሆነችው አገሪቱ ባላት ከነዳጅ ዘይት ኢንዱስትሪ የተያያዘ የታወቀ የትምህርት ሥርአት ምክንያት ነበር፡፡ እንደ አዘርባጃን አለማቀፍ ጆርናል (በጋ 2002) አዘርባጃን ለክፍለ ዘመናት እንዲያውም ለሺ ዘመናት ከነዳጅ ዘይት ኢንዱስትሪ ትስስር ነበራት፡፡ የመካከለኛ ዘመን የክልሉ ተጓዦች አገሪቱ ያላትን የተትረፈረፈ የነዳጅ ዘይት ኃብትና ይህ ኃብት የሕዝቡ የእለት ተእለት ሕይወት አንድ አካል መሆኑን በጉዞ ማስታወሻቸው አስፍረዋል፡፡

በ19ኛው ክፍለ ዘመን አዘርባጃን በአለም የነዳጅ ዘይትና ጋዝ ኢንዱስትሪ ከሁሉም አገሮች መሪ ነበረች፡፡ በ1846 አሜሪካኖች ታዋቂ የነዳጅ ዘይታቸውን በፔንሲልቫኒያ ከማግኘታቸው በፊት ከአንድ አስርት ዓመታት በላይ አዘርባጃን በቢቢ-ሄባት የመጀመሪያውን የነዳጅ ዘይት ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ አከናውናለች፡፡ በ20ኛው ክፍለ ዘመን አዘርባጃን ከአለም የነዳጅ ዘይት አቅርቦት ከግማሽ በላይ አምራች ነበረች፡፡

በዚህ መሠረት በተለይ በሶቪየት ሕብረት ዘመን በአዘርባጃን ከነዳጅ ዘይት ኢንዱስትሪ ለተያያዘ የትምሕርት ሥርአት የተሰጠው ትኩረት ምክንያታዊ ነበር፡፡ በዚሁ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት በተለይ በ70ዎቹና በ80ዎቹ ከነዳጅ ዘይት በተያያዘ ኢንዱስትሪ በተለይም በፍለጋ አካባቢ ኢንቨስት የማድረግ ስትራቴጂ ነበረው፡፡ እንደ ስትራቴጂያዊ አጋር ሶቪየት ሕብረት በትምሕርትና አቅም ግንባታ በየጊዜው ብዙ ስፔሻሊስቶችን በዘርፉ ለማሰማራት የመጀመሪያ ተመራጭ አገር ነበረች፡፡

ከነዳጅ ዘይት ኢንዱስትሪ ተያያዥነት ካለው ትምህርት በተጨማሪ ከወታደራዊ የማሪያን አካዳሚ ትምህርት ቤቶች የተመረቁ፣ እንዲሁም ጂኦሎጂስቶች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ የሕክምና ዶክተሮች. መካኒካልና ሲቪል መሐንዲሶችና በሌሎች ስፔሻላይዜሽን መስኮች ስልጠና የወሰዱ በርካታ ኢትዮጵያውያን አሉ፡፡

በአዘርባጃን ለመማርና ለመኖር እድል ካገኙ ዜጎች አንዱም እኔ ነኝ፡፡ በ1989 በጋ ወደ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አዘርባጃን ሄድኩ፡፡ የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ እንዲሁም በ2005 የፒኤችዲ ትምህርቴን አጠናቅቄ እስከ 2010 በአዘርባጃን መሥራትና መኖር ቀጠልኩ፡፡ በዚያው አገር ሕይወት ከ21 አመት ቆይታ በኋላ ለበጎ ፈቃድ ወደኢትዮጵያ ተመለስኩ፡፡ ኢትዮጵያዊት ሚስቴንም ለማግኘት ታድያለሁ፣ እርሷም እኔ በሄድኩበት በዚያው አመት ለትምህርት ወደአዘርባጃን የሄደችው፡፡ በባኩ የተወለዱ ሁለት ሴት ልጆች አፍርተናል፡፡

ምስል 1፡ የዲሴምበር 1989 የባኩ የመጀመሪያ የበረዶ ተሞክሯችን

# የአዘርባጃን ቅኝት



በአዘርባጃን ለኖርን ኢትዮጵያውያን ምቾት የሚሰጠን በባህልና በኃይማኖት ብዝኃነት ዙሪያ ያለን የጋራ እሴት ነው፡፡ ከኢትዮጵያ በተመሳሳይ ሁኔታ አዘርባጃን ለሺዎች ዘመናት የተለያዩ ኃይማኖቶችና ባህሎች ስብጥር የደመቀች አገር ነበረች፣ አዘርባጃኒዎች ባላቸው የመቻቻል ባህል የሚኮሩ ናቸው፡፡ ይህ ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መሆኑን የሚያስቡ ብዙ ሰዎች ያሉ በመሆኑ ብሔራዊ መለያቸው መሆኑም ይታመንበታል፡፡ የመቻቻል የጋራ መገለጫ አዘርባጃኒዎች ከማንኛውም እምነት አስተምህሮ በላይ ለብሄራዊ ማንነታቸው ዋጋ የሚሰጡ ናቸው የሚለውን ሃሳብ ይጨምራል፡፡ በታሪክ የአዘርባጃን ሕዝብ የተለያዩ ኃይማኖቶችና እምነቶች የሚከተል ነው፣ ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ ዞሮአስትሪያኒዝም (የእሳት አምልኮ)፣ ክርስትና (በዋነኘነት ከ3ኛው እስከ 4ኛው ክፍለ ዘመን ክርስትናን እንዲሁም አናሳ የአካባቢ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮችንና የሩስያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን ጨምሮ) እና እስልምና ናቸው (ከ6ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ባሁኑ ጊዜ አብዛኞቹ አዘርባጃኒዎች ሙስሊም ነን ብለው የሚያምኑ ሲሆን የአዘርባጃን ሪፐብሊክ ግን አለማዊ አገር ነች)፡፡ ኢትዮጵያውያን የኃይማኖት፣ የጾታ ወይም የእድሜ ልዩነት ቢኖርም በአገሪቱ ሕዝብ ተቀባይነት አላቸው፡፡

አንድ ኢትዮጵያዊ ማየት የሚችለው የመጀመሪያ ነገር “አልማዝ” የሚል የሴት መጠሪያ ስም የምንጋራ መሆኑ ነው፡፡ በግል እኔ ይህን ስም ለመጀመሪያ ጊዜ በባኩ ስሰማ ተደንቄያለሁ፡፡ በአማርኛና በአዜሪ ቋንቋዎች መካከል ምናልባትም በተመሳሳይ የአረብኛ ቋንቋ ምንጭ ምክንያት የምንጋራቸው ሌሎች በርካታ በርካታ የጋራ ቃላትም አሉ፡፡ የባኩ የግንብ ከተማም ከሐረር የግንብ ከተማ (ጀጎል) በጣም ተመሳሳይ ናት፣ የአዘርባጃን ሕዝብ (አዛሪ) ከሐረር የግንብ ከተማ ሕዝብ (ከአደሬዎች) የሚያመሳስሉት ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመረዳት ተጨማሪ ምርምር የሚጠይቅ ሲሆን በግል የሆነ ግንኙነት መኖር እንዳለበት አምናለሁ፡፡ በመሆኑም ይህ ለተጨማሪ ምርምር መነሻ ሊሆን የሚችል አንድ አካባቢ ሊሆን ይችላል፡፡

ብዙ ኢትዮጵያውያን በአዘርባጃን ከፍተኛ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደአገራቸው ተመልሰው በተለያዩ ቁልፍ የሥራ ቦታዎች በባለሙያነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፤ እነዚህም ከፍተኛ በማዕድንና ኤነርጂ ሚኒስቴር፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በማዘጋጃ ቤት (የአዲስ አበባን ጨምሮ)፣ በፍርድ ቤቶች ሥርአት፣ በመያዶች አመራር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዲሁም በግል የንግድ ድርጅቶች፣ የአገር ውስጥና አለማቀፍ የሕግ ቢሮዎችን፣ የማማከር አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ወዘተ በከፍተኛ የሥራ ቦታዎች የሚሰሩትን ባለሙያዎች ይጨምራሉ፡፡ በኢትዮጵያ የአዘርባጃን ኤምባሲ ባለፉት ሁለት አመታት የቀድሞ የአዘርባጃን ተማሪዎችን ማኅበር ለማቋቋም የሚደረጉ ጥረቶችን ሲያስተባብር



ቆይቷል፡፡ የማኅበሩ ዋና አላማ በኢትዮጵያና በአዘርባጃን መንግሥታት መካከል በተለይ በሳይንስ፣ በትምሕርት፣ በባህልና በኤነርጂ መስኮች ያለውን ግንኙነት ለማሳደግ አስተዋጽኦ ማድረግ መሆኑ ይታመንበታል፡፡

በዚሁ ጊዜ በሁለቱ አገሮችና ሕዝቦች መካከል ላለው ታሪካዊ ግንኙነት ለጋራ እሴቶችና አቅሞች እውቅና በመስጠት ጠንካራ ትብብር ከመፍጠር አንጻር አሁንም ገና ብዙ መሠራት ያለበት ይመስለኛል፡፡ አዘርባጃንና ኢትዮጵያ የሚያመሳስሏቸው በርካታ ነገሮች እንዳሉ፣ በሁለቱ አገሮች መንግሥታትና ሕዝቦች መካከል ያለውን አጋርነት በላቀ ደረጃ ለማስፋፋት ያላሰለሰ ጥረት መደረግ እንዳለበት ጠንካራ እምነት አለኝ፡፡

በአዘርባጃን የነበረንን የሕይወት ተሞክሮ በሚመለከት ለተጨማሪ መረጃ በመጀመሪያው የአማርኛ አይአርኤስ (ቅርስ) ጆርናል እትም ታትሞ የወጣውን መጣጥፍ (http://irs-az.com/new/am) ማንበብ ይችላሉ፡፡

**(የተርጓሚው ማስታወሻ፡- በዚህ መጣጥፍ የተጠቀሰ ዘመን ሁሉም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው፡፡)**

